## መመሪያ ቁጥር.06./2010

### ልውጥ ሕያዋን ላይ በሚደረጉ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች በተያያዘ ሊደርስ የሚችል ጠንቅ መቋቋሚያ የአሰራር ሥርዓት መመሪያ

ከልውጥ ሕያዋን እንቅስቃሴዎች በተያያዘ ሊደርሱ የሚችሉትን ድንገተኛ አደጋዎችን ለመከላከል የሚያስችል የጠንቅ መቋቋም አሰራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የአካባቢ፣ የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ስለደሕንነት ሕይወት በወጣው አዋጅ ቁጥር 655/2001 (በአዋጅ ቁጥር 896/2007 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 25 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "ከልውጥ ሕያዋን እንቅስቃሴ ጋራ የተያያዘ ጠንቅን የመቋቋሚያ የአተገባበር ሥርዓት ለመዘርጋት የተዘጋጀ መመሪያ ቁጥር 06/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **የተፈፃሚነት ወሰን**

(1) ይህ መመሪያ ለተጤነ እና ላልተጤነ ልቀት፤ ልውጥ ሕያዋን ለመሥራት፣ ለማስተማሪያነት፣ ለምርምር፣ ከውጪ ለማስመጣት፣ ወደ ውጪ ለመላክ፣ በትራንዚት ለማስተላለፍ፣ በዝግ ሁኔታ ለማምረት፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ፣ በጥሬ ዕቃነት ለማዋል እና በገበያ ላይ በማዋል ጊዜ ሊፈጥር በሚችለው ጠንቅ ላይ ተፈፃሚነት ይኖራዋል፡፡

(2) በዚህ መመሪያ በሌላ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር ካልተጤነ ልቀት የሚመነጩ ጠንቆች ያሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

ሀ/ በማከማቸት ወይም በማጓጓዝ ወቅት የሚንጠባጠቡ፣

ለ/ በሰዎች ስህተት የሚለቀቁ፣

ሐ/ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የሚለቀቁ

## ክፍል ሁለት

3. ከማንኛውም እንቅስቃሴ የሚመነጩ ጠንቆችን የመቋቋሚያ ምላሽ

(1) ማንኛውንም ፍቃድ ጥያቄ ሲቀርብ ሚኒስቴሩ ፍቃድ ከመስጠቱ በፊት ጥያቄው የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተቱትን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ሀ/ ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚወሰዱ እርምጃዎች መረጃ እና የአተገባበር ስልትን ያጠቃለለ የአደጋ መቋቋሚያ ጊዜ እቅድን ማዘጋጀት እና

ለ/ በእንቅስቃሴው ጉዳት ሊደርስበት የሚችል ሰው/ሰዎች ቢኖሩ መረጃ የሚያገኙበት ዕቅድ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

4. የድንገተኛ አደጋ መከላከል ግብረ ሃይል

(1) ማንኛውም የልውጥ ሕያው እንቅስቃሴ ሲደረግ የሚያጋጥም ድንገተኛ አደጋን ለመቋቋም እንዲቻል የአደጋ መከላከል ግብረ ሀይል ሚኒስቴሩ ይሰይማል፡፡

(2) ሚኔስቴሩ የድንገተኛ አደጋ መከላከል ግብረ ሀይል ሊቀመንበርን፣ ጸሐፊንና አባላትን የድንገተኛ አደጋን የመቋቋሚያ እርምጃ መውሰድ አቅም ካላቸው ተቋማት መካከል ይሰይማል፡፡

(3) የድንገተኛ አደጋ መከላከል ግብረ ሀይል ኃላፊነቶችና ተግባራት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው፤

ሀ/ ብሔራዊ የአደጋ መቋቋሚያ እቅድን ማዘጋጀት፣ ሲያስፈልግ መተግበርና በየጊዜው ማሻሻል፤

ለ/ ማንኛውም ከልውጥ ሕያው እንቅስቃሴ የሚደርስ ያልተጤነ ልቀት መከሰቱን ለመለየትና ለመዘገብ የሚያስችሉ ተገቢ ስርዓቶችን መዘርጋት፤

ሐ/ ከልውጥ ሕያዋን ያልተጤነ ልቀት ሊመጣ የሚችለውን በሰው ወይም በእንስሳት ጤንነትና በአካባቢ የሚደርስ አደጋን ለመከላከል የሚያስችል ፈጣን የመቋቋሚያ ስልት ምንጊዜም ዝግጁ መሆኑን ማረጋገጥ፤

መ/ የልውጥ ሕያዋን ያልተጤነ ልቀት በሚያጋጥምበት ጊዜ በሰው ወይም በእንስሳት ጤንነት እና በአካባቢ ጉዳት ሳይደርስ ለውጥ ሕያውን ለማስወገድ በቂ ዝግጅት ምንጊዜም መኖሩን ማረጋገጥ፤

ሠ/ ወጪዎችን ለማስመለስና ካሳን ለማስከፈል እንዲያግዝ የአደጋ መቋቋሚያ እርምጃ በሚወሰድበት ጊዜ የሚደርሱ ወጪዎችን በተሟላና በትክክለኛ መንገድ መመዝገባቸውን ማረጋገጥ፤

Ministry of Environment, Forest and Climate Change

ረ/ ያልተጤነ ልቀትን መቋቋም የሚያስችል የሰው ኃይል፣ ገንዘብና መሣሪያ ዝግጁ መሆኑን ማረጋገጥ፤

(4) የድንገተኛ አደጋ መከላከል ግብረ ሀይል በአገር አቀፍ ደረጃ የሚያጋጥም ማናቸውንም ልውጥ ሕያዋንን የሚመለከት አደጋ የመምራት እና ለመቋቋም የሚያግዙ ድርጅቶችና ግለሰቦችን የማስተባበር ኃላፊነት አለበት።

(5) የድንገተኛ አደጋ መከላከል ግብረ ሀይል የተሰጡትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ለመወጣት እንደአስፈላጊነቱ በሚወስነው ሰዓትና ፍጥነት መገናኘት የሚችል ሲሆን ነገር ግን ከ6 ወር በላይ መብለጥ አይኖርበትም።

(6) በልውጥ ሕያዋን ያልተጤነ ልቀት አማካኝነት ድንገተኛ አደጋ በሚደርስበት ጊዜ የድንገተኛ አደጋ መከላከል ግብረ ሀይል ኃላፊነት ከተሰጠው ሰው እና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋራ በቅርብ በመሥራት አደጋውን መቀነስ ወይም ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ይኖርበታል።

(7) የዚህን መመሪያ አንቀፆች እንደተጠበቁ ሆነው የድንገተኛ አደጋ መከላከል ግብረ ሀይል የራሱን የአደጋ ጊዜ መቋቋሚያ የአሰራር ሥራዓቶችን ማውጣት ይችላል።

## 5. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ኃላፊነቶች

(1) በልውጥ ሕያዋን እንቅስቃሴዎች ወቅት አደጋ ቢያጋጥም፣ ማንኛውም አመልካች ወይም ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው፣ አደጋው ባጋጠመ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ፣ ለአደጋ መቋቋሚያ ቡድኑ የሚከተሉትን መረጃዎች መስጠት ይጠበቅበታል፡-

ሀ/ አደጋው የደረሰባቸው ሁኔታዎች፣

ለ/ አደጋው ሲከሰት የነበረው ልውጥ ሕያው ምንነትና መጠን፣

ሐ/ ማንኛውንም በብዝሀ ሕይወት ጥበቃና ዘላቂ አጠቃቀም እና በሰዎች ጤንነት ላይ ሊያደርስ የሚችለው አሉታዊ ተፅእኖ የሚገልፅ መረጃ፣

መ/ የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች፣ እና

ሠ/ ሌሎች ማንኛውም ተያያዥ መረጃዎች።

## 6. በአመልካቹ መወሰድ የሚኖርባቸው የጠንቅ አያያዝ እርምጃዎች

(1) አመልካቹ ወይም ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው ግለሰብ አደጋዎች በሚደርሱበት ወቅት የሚከተሉትን የጠንቅ አያያዝ ተግባራትን ማከናወን ይጠበቅበታል፡-

ሀ/ ለድንገተኛ አደጋ መከላከል ግብረ ሀይል ሪፖርት ማድረግ፣

ለ/ ለአካባቢው አመራር መረጃዎችን በመስጠት አካባቢው እንዲጠበቅ ማድረግ እና ለሕብረተሰቡ ግንዛቤ መስጠት፣

ሐ/ ቦታው ተለይቶ እንዲከለል አድርጎ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጠበቅ ማድረግ፣

መ/ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ አደጋው ከደረሰበት ቦታ ላይ ደረጃ በደረጃ ሰዎችንና እንስሳትን ከቦታው እንዲለቁ ማድረግ፣

ሠ/ ከልውጥ ሕያዋኑ አደጋ መከሰት ጋር በተያያዘ በትርፍነት/ዝቃጭነት በቦታው ላይ የሚቀሩ ነገሮች ካሉ መሰብሰብና፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም፣ ተገቢ በሆነ መንገድ እንዲወገዱ ማድረግ።

## 7. የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ...[illegible]...፰..ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ.....[illegible]..፰..ቀን 2010 ዓ.ም

ዶ/ር ገመዶ ዳሌ
የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ
ሚኒስቴር ሚኒስትር

**DIRECTIVE NO.06/2018**

## DIRECTIVE TO ESTABLISH PROCEDURES FOR MANAGEMENT OF RISKS FROM ANY TRANSACTION INVOLVINGMODIFIED ORGANISMS

**Whereas,** it is essential to set a risk management procedure dealing with risks arising from any transaction involving modified organisms,

NOW THEREFORE, this directive is issued by the Ministry of Environment, Forest and Climate Change in accordance with Article 25 of the Biosafety Proclamation No. 655/2009 (as amended by Proclamation No. 896/2015):

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This directive may be cited as ''Directive Issued to Establish Procedures for the Management of Risks from any Transaction Involving Modified Organisms No.06/ 2018"

### 2. Scope of this Directive

(1) This Directive shall apply to manage any unforeseen risk arising from deliberate and unintentional release during making, use in teaching, research, import, export, transit, contained production, transport, storage, processing and putting in the market of any modified organisms.

(2) In this directive, unless the context otherwise requires, the Risk arising from unintentional release includes, *inter alia*;

a. Spillage from storage or transportation,

b. release out of Human error

c. Release out of force majeure.

Ministry of Environment, Forest and Climate Change

## PART TWO

### 3. Response Measures To Risks Arising From Any Transaction

(1) The ministry shall, before recommending an application for approval for any transaction, ensure that the application contains;

a. An emergency plan which includes information on safety measures and procedures to be adopted and,

b. Mechanisms through which the information shall be made available to the persons likely to be affected by the transaction.

### 4. Emergency Response Group

**(1)** The Minister shall establish an Emergency Response Group in order to respond to any emergency cases related to the transaction of modified organism.

**(2)** The Minister shall appoint the Chairperson, the Secretary and the members of the Emergency Response Group to comprise representatives of institutions capable of undertaking risk management measures.

**(3)** The duties and responsibilities of the Emergency Response Group shall be to:

a. Develop, implement when needed and keep updating a national risk management plan;

b. Develop appropriate systems for the detection and reporting of emergencies in any transaction involving modified organisms;

c. Ensure that there is a constant readiness to respond to any emergency of any modified organism to prevent damage to human and animal health, and the environment.

d. Ensure that there is a constant readiness for the disposal of modified organisms recovered after accidents without any harm to humans, animals or the environment;

e. Ensure that complete and accurate records of expenditures incurred in responding to emergencies are maintained to facilitate cost recovery and the payment of compensation;

f. Ensure prompt and efficient mobilization of manpower, financial resources and equipment to deal with any emergency;

(4) The Emergency Response Group shall be responsible to coordinate any accident at national level involving modified organisms and it shall direct the activities of institutions and individuals that may offer assistance.

(5) The Emergency Response Group shall meet at such times and with such frequency as may be necessary to fulfill its duties and responsibilities which, in any event, shall not be less than every six months.

(6) In cases of emergencies such as accidental release of modified organisms, the Emergency Response Group shall closely work with the authorized person and other relevant stakeholders to take rapid action to minimize or prevent possible risks

(7) Without prejudice to the provision of this article, the Emergency Response Group may adopt its own rules of procedures.

**5. <u>Duties of the Permit Holder</u>**

(1) Where there is an emergency related to transaction of modified organisms, the applicant or any person to whom approval was given shall, within twenty-four hours, inform the Emergency Response Group about the emergency providing the following information-

a. The circumstances of the accident,

b. The identity and quantity of the modified organism involved in the emergency,

c. Any available information about the possible adverse effects on the conservation and sustainable use of biological diversity, taking also into account risks to human health,

d. The mitigation measures taken, and

e. Any other relevant information.

**6. <u>Risk management measures to be taken by the applicant</u>**

(1) The applicant or any person to whom approval was given shall use the following Risk Management approaches in the event of emergency

a. Report to the Emergency Response Group.

b. Inform and involve the local leadership to take charge of the area and create awareness to the population.

c. Isolate the area and provide adequate security to cordon off the affected place, if needed.

d. When appropriate, evacuate humans and animals that are within reach by the exposure case by case.

e. In the event where there are residual materials arising from modified organisms, they have to be collected and, when applicable, be destroyed by appropriate means.

**7. Effective Date**

This directive shall enter into force as of the 16/01 day of 2018.

Done at Addis Ababa, this 16 day of Jan 2018.

Dr. Gemedo Dalle

MINISTER OF MINSTRY OF ENVIRONMENT, FOREST AND CLIMATE CHANGE